አርበኞች ግንቦት 7 የአንድነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ፣

Patriotic Ginbot7 Movement for the Unity and Democracy

ቀን 17/05/2011 ዓ/ም

ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የትጥቅ ትግል በማቆም ወደ ሰላማዊ ህይወት የሚመለሱ አባሎችን መልሶ ማቋቋምን ይመለከታል።

ከሁሉ በማስቀድም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በተመረጡ በወራት እድሜ ውስጥ ፤ እርሶ የሚመሩት መንግስት ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ይሆናሉ ተብለው የማይገመቱ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑንና የተጨበጡ ወጤቶችን ማስመዝገቡን በከፍተኛ አንክሮ የምገነዘበው ሲሆን ላስመዘገቡት ውጤትም ያለኝን ከፍተኛ አድናቆት ሳልገልጽ ለማለፍ አይቻለኝም። አገሪቷን የማረጋጋትና የህግ የበላይነትን በማስጠበቅ እንዲሁም ያልተመለሱ ጥያቄዎችን መፍትሄ በመስጠት፤ የተመዘገበው ውጤትም ወደ ኋላ እንዳይመለስም የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ሁላችንም ለላቀ ስራ ልንተጋ ይገባል እላለሁ።

ይህንን ማስተወሻ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት፤ ከመንግስት የቀረበው የሰላም ጥሪ ተከትሎ ንቅናቄያችን ከመንግሰት ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት፤ ለኢትዮጵያና ለህዝቧቿ የሚገባውን ሰላም፣ ዲሞክራሲና፣ ልማት እውን ለማድረግ ሲካሂድ በነበረው ሁለገብ ትግል፤ ሁሉ ነገራቸውን አሳልፈው ሰጥተው የህይወት መስዋትነት ጭምር ለመክፈል ሲታገሉ የነበሩትን አባሎቻችንን ወደ ሰላማዊ ህይወት የመመለስ ጥረት በተፈለገው ሁኔታ አለመካሄዱ የሚስከትለው ችግር የፈጠረብኝ ስጋት ነው።

በአሁኑ ግዜ የተወሰኑት አባሎቻችን በጎንደር ወረታ ካምፕ ያሉ ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው ተጠግተው ኑሮአቸውን እየገፉ ይገኛሉ።የተቀሩት ደግሞ በአሉበት ሆነው የመልሶ ማቋቋሙ መርሃ ግብር መጀመርን በአሰቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ሆነው በመጠባባቅ ላይ ናቸው።ለአብነትም ያህል ከሁለት ሳምንታት በፊት በወረታ ካምፕ፣ ጎንደር ከሚገኙ አባሎች ጋር ባደረኩት ውይይት በካምፕ ውስጥ ከሚሰጥ ዕለታዊ ድጋፍ አልፎ ለዘሌቄታ በሚሆን መልኩ የአገሪቱን አቅም ባገናዘበ ሁኔታ እንኳን፤ የመኖሪያ ሥፍራንና ለመተዳደርያ የሚሆን ገቢ ሊኖረን ይገባል በሚል ከፍተኛ ምሬት ላይ ቅሬታቸውን አስተጋብተዋል።

እነዚህ በካምፕ ውጭና በወሮታ ካምፕ ውስጥ የሚገኙ የቀድሞ ታጋዮች ተስፋ ቆርጠው ዳግመኛ በረሃ ሊወጡ የሚችሉበት ሁኔታም እንዳይፈጠርና አገሪቱ ውስጥ ያለውን የጸጥታ ችግር እንዳያባበስ ከፍተኛ ሰጋት አድሮብኛል። ይህን የምልበት ሌላው ምክንያት ፡ ለምሳሌ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል (አድሃን) የሚባለው ከኤርትራ የገባው የትጥቅ ትግል ሲያደርግ የነበረ ድርጅት አመራሮችና ታጋዮች በአማራ ክልል የአስተዳደር፣ የደህንነት፣ የልዩ ሃይልና የሚሊሺያ ውስጥ ተደልድለዋል። በአንጻፉ በኢትዮጵያዊነት የተደራጁትና ህብረ ብሄራዊ ስብጥር ያላቸው የአግ 7 ታጋዮች እስካሁን ወደ ሰላማዊ ኑሮቻው እንዲገቡ

የተደረገ ስልጠናም ሆነ ድጋፍ ምንም አልተጀመረም። ይህ ሁኔታ ምን አይነት አደገኛ ስሜት እየፈጠረ መሆኑን፡ ጭራሹኑም በኢትዮጵያዊነት ስለተደራጀሁ፣ ለአንድ ብሄር ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ በታገልኩ ተጣልኩ፣ ተረሳሁ ወደሚሉ መጥፎ ስሜቶችን ምሬት በማበረታት ሁሉም ወደ የብሄሩ እንዲመሸግ የሚያበረታታ ሁኔታ እየወለደ መሆኑን በወሮታ ካምፕ ውስጥም ሆነ በውጭ ሆነው ስልጠና እንዲሁም ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲገቡ የሚያግዝ እርዳታ የሚጠባበቁትን ታጋዮች በማነጋግርበት ጊዜ የተረዳሁት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ነው።

እነኚህ አባላት ቀደም ሲል የነበራቸውን ኑሮ በትነው ወደ ትጥቅ ትግል ጎራ ሲቀላለቀሉ የነበራቸውንና ሊኖራቸው ይችለው የነበረውን ነገር ሁሉ ለትግሉ ሲሉ ያጡ መሆናቸው ይታወቃል። ለሃገራችንን ለህዝባችን ጥቅም ሲሉ በአመኑበት መሥመር በቁርጠኝት የታገሉ እንደመሆናቸውና፤ ለለውጡም የበኩላቸው አስተወጽዖ የማድረጋቸውን ያህል መሠረታዊ ፍላጎታቸው ለዛሬና ለነገም ጭምር እንዲሟላላቸው ማድረግ ጊዜ የሚሰጠው ተግባር አይሆንም። መንግስት በብዙ አጣዳፊ ሁኔታዎች የመያዙ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እነዚህ በመቶና በሺህ የሚቆጠሩ አንስተኛ ቁጥር ያላቸውን ዜጎች በልዩ ሁኔታም ቢሆን የሚታገዙበት ሁኔታ ማመቻቸት የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት አለኝ። ለአመኑበትና ለአገራዊ ትልቅ አላማ በቁርጠኝነት መሰለፍ የሚያስከብር መሆኑን በተግባር ማሰየትና ማረጋገጥ የሚያስተላልፈው አወንታዊ መልዕክቱም ቀላል አይሆንም። በተቃራነው ይህ አለመሆኑ አሉታዊ መልዕክቱም የዛኑ ያህል አደገኛ አደጋ ያዘለ ይመስለኛል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር፥-

ለታጋዮቻችን መልሶ ማቋቋሚያ የሚያስፈልገውን ድጋፍ፤ ለማሰባሳብ፤ እርሶ ባሎት ግንኙነት ሁሉ ለሚመለከታቸው ለጋሽ መንግስታት በቀጥታና በአምባሳደሮቻቸው በኩል እንደሚያስታውቋቸው፤ በእርሶ መንግስት የሰላም ጥሪ ወቅት ከእኛ ድርጅት ጋር በአሜሪካ አገር ባደረግነው ውይይት የገቡልንን ቃል እስታውሳለሁ። ከንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ከዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስለዚሁ እንዲሁም በሌሎች ሀገራዎ ጉዳዮች ከእርሶ ጋር የሚደረጉትን ምክክሮች እከታተላለሁ።

በንቀናቄችንም በኩል ይህ የመልሶ ማቋቋምን ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው እንደመሆኑ፤ በዋና ጸኃፊያችን በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚመራ ቡድን፤ ባለፉት አምስት ወራት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እንቀስቃሴ ሲያድርግ ቆይቷል። በተለይም በአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራሮች የሆንና አባላቱ በግልና በቡድን የአለውን ዓለም አቃፋዊ ግንኙነት በመጠቀምና ለዚሁ ስራ ተቋቋሞ በተሰማራ አፍሪድ በተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በአጋርነት በእርሶ ጽ/ቤት ስር የተቋቋመው የመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያደርገውን የሀብትን ማሰባሰብን ሂደት ለማፋጠን ቡዱኑ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎአል። ይሁንና ከመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተቀናጅቶ የሚሰራበት ሁኔታ ባለመመቻቸቱ ይህ ግዜ ሊሰጠው የማይገባ ተግባር እነሆ ላለፉት አምስት ወራት ያለምንም ተጨባጭ ውጤት በመዘግየቱ ጉዳዩን ለእርሶ ለማቅረብ ተገድጃለሁ። ይህ ጉዳይ የንቅናቄውን ሊቀመንበር እንዲሁም ዋን ጸሃፊ ብቻ ሳይሆን በንቅናቃው ውስጥ በአመራር ላይ የምንገኘውን ሁሉ የሚመለከት የጋራ ሃላፊነት ያለብን በመሆኑ ነው።

በቅርቡም ከሁለት ሳምንታት በፊት ጎንደር በወሮታ ካምፕ ተገኝቼ ከታጋዮች ጋር ካደረኩት ውይይት በኋላ በመልሶ ማቋቋም ተግባር ሀጋራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ልምድ ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮሪጊስ፤ የንቅናቃው ዋና ጸኃፊ አቶ አንድአርጋቸው ጽጌ፤ አቶ ቴዎድሮስ ይልማ የአፍሪድ ሥራ አሥኪያጅንና እኔ በመሆን፤ ከአቶ ተስፋዬ ይገዙ የመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር ተገናኝተን ሰፊ ምክክር አካሂደን ነበር።

በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የርሶን ጣልቃ መግባት፣ ግልጽ መመሪያና ውሳኔ የግድ እንደሚያስፈልግ መግባባት ላይ ተደርሷል። ሰለሆነም ፦

1. በእርሶ ጽ/ቤት ስር የተቋቋመው የመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስካሁን የተጓዘበት ሁኔታ ተገምግሞ ሥራው ተጠናክሮ የሚፋጠንበት ሁኔታ ቢመቻች።

2. ንቅናቄችን እና የመልሶ ማቋቋም ፕሮጄክት ጽ/ቤት ተቀናጅቶ የሚሰራበት ሁኔታ እንዲመቻች የሁለትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረምና ሥራው በዚሁ ሁኔታ እንዲፋጠን፡፡

3. ከፍተኛ ፈቃደኛ ባለሙያዎችን በማሳበሰብ ሊያግዘን የተቋቋመው አፍሪድ የተሰኘው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እና የመልሶ ማቋቋም ፕሮጄክት ጽ/ቤት ተቀናጅተው የሚሰሩበት ሁኔታ እንዲመቻች የሁለትዮሽ እንደ አስፈላጊነቱ የሦሥትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ እንደፈረምና ሥራው በዚሁ ሁኔታ እንዲፋጠን ቢደረግ ::

4. ለመልሶ ማቋቋሙ የሚውል የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ለማሰባሰብ እንዲረዳ፤ በድርጅቱና በአባላቱ በግልና በቡድን የአለውን ዓለም አቃፋዊ ግንኙነት በመጠቀም ንቀናቂያችን ለዚሁ ተግባር ሊያግዘን ከተቋቋመው አፍሪድ ከተሰኘው መያድ ጋር በአጋርነት ለምናከናውነው እንቀስቃሴ ለዚሁ ተግባር ከለጋሽ መንግሰታትና ድርጅቶች የሚፈለገውን ተገቢ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጸፋልንና ተገቢው ድጋፍ ቢደረግ።

ከላይ የተዘረዘሩትን በታላቅ ትህትና ስንጠይቅ የጉዳዩን አሳሳቢነትና ግዜ አይሴጤነት የሚመጥን እርምጃ እንደሚወስዱ ከአደረብኝ ጽኑ እምነት በመነሳት ነው፡፡ ከእርሶ ጋር ቀጠሮ ተይዞ በዚህ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር በመሆን ለማቅረብ የበኩሌን ሙከራ ባደርግም ካለቦት የስራ መደራረብና ውጥረት ሳቢያ ሊሆን እንዳልቻለ ተረድቻለሁ። ወደ አሜሪካ ተመልሶ የመሄጃ ቀን በመድረሱም በመሆኑ ይህን እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ በጽሁፍ እንዲደርሶ ለማድረግ ተገድጃለሁ።

ከከፍተኛ የአክብሮት ሰላምታ ጋር ፦

ነዓምን ዘለቀ፡ - የአርበኞች ግንቦት 7 የሥራ አስፈጻሚ አባልና የውጭ ጉዳዮች ኃላፊ

ግልባጭ ፦

ለአቶ ተሰፋዮ ይገዙ፡ - ለመልሶ ማቋቋም ፕሮጅክት ጽ/ቤት ሃላፊ
ለዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፦ የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀመንበር
ለአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፦ የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ
ለአርበኞች ግንቦት 7 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት
ለአቶ ቴዎድሮስ ይልማ፦ ለአፍሪድ ዋና ሰራ አስኪያጅ
ለሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮሪጊስ